# የወተት ፍጆታችን ለምን ዝቅተኛ  ሆነ?

**የዋጋ ጉዳይ?**

ወተት አንጻራዊ ዋጋ ከሌሎች ምግብነት ይዘት ካላቸውም ሆነ ከሌላቸው ነገሮች ጋር ሲነጻጸር ርካሽ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ከባለ አንድ ሊተር የታሸገ ውሃ፤ ጭማቂ፤ለስላሳና አልኮልነት ካላቸው ነገሮች ጋር የዋጋና የምግብነት ይዘት ንፅፅሩን ቢሰሩ ወተት ምን ያህል ርካሽ እንደሆነ በቀላሉ ይረዱታል፡፡

**አለመገኘት?**

በእርግጥ አጠቃላይ አመታዊ የወተት ምርት መጠን ከላሞች 3.8 ቢሊዮን ሊትር ከግሞሎች 165.12 ሚሊዮን ሊትር ብቻ እደሆነና አንድ ላም በአማካይ የምትታለበው የወተት መጠንም ከ 1.32 ሊትር እንደማይበልጥ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ሰታትስቲክስ (CSA 2004) ገምቷል፡፡ ምርታማነትን ከመጨመር አኳያ ብዙ መሰራት ያለበት መሆኑ እንዳለ ሆኖ ወተት አምራቾች ለዚች ውስን ምርት እንኳ የገበያ ችግር እንደሚያጋጥማቸው በተለያዩ ጊዜያት ይገልጻሉ፡፡

**ጥቅምን አለማወቅ?**

ወተት የጎለበተ አካል፤ ብሩህ አእምሮ፤ ጤነኛና አምራቾች ዜጋን ለማፍራት ያለው ፋይዳ ወደር የለውም፡፡  ወተት በሁሉም የእድሜ ክልል  ላሉ ሰዎች ተወዳዳሪ የማይገኝለት ምግብ ነው፡፡ ይህ ግንዛቤ በብዙዎቻችን አእምሮ ውስጥ ከሰረጸና ተቀዳሚ ምርጫችን  ወተት ከሆነ፡ አካላችን ጠንካራ፤ አእምሮአችን ብሩህ ጤንነታችን የተጠበቀ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡ ተጠቃሚ ከጨመረ ደግሞ የወተት ገበያ ይስፋፋል፤ አምራቹ ይበረታታል፤ የወተት ምርትና ምርታማነት ያድጋል፤ ዋጋውም ተመጣጣኝ ይሆናል፤ የተለያዩ የወተተ ዉጤቶችም ለገበያ መቅረብ ይጀምራሉ፡፡ የዓለም የትምህርት ቤት የወተት ቀንም ከፈረንጆች 2000 ዓ.ም. ጀምሮ በየዓመቱ የሚከበረው የወተት ጠቃሜታን ግንዛቤ በተማሪዎችና በሌሎች ማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ለማስረፅና ይህንን ተተኪ የሌለው  የወተተ ተጠቃሚነትን በመጨመርና አምራቹም ተበራቶ የወተት ልማት ዘርፍ የሚጠናከርበት መንገድ ለመቀየስ  ነው፡፡




**LIVES project**

**Tele. 215-58-218-01-79**

**Bahir Dar, Ethiopia**

# የዓለም ትምህርት ቤቶች የወተት ቀን

## የእንስሳትና የመስኖ እርሻ እሴት ሰንሰለት ልማት ፕሮጀክት

Livestock and Irrigation Value chains for Ethiopian Smallholders

**LIVESTOCK AND IRRIGATION VALUE CHAINS FOR ETHIOPIAN SMALLHOLDERS PROJECT( LIVES)**

2006ዓ.ም. (2013 G.C.)

## የእንስሳትና የመስኖ እርሻ እሴት ሰንሰለት ልማት ፕሮጀክት ( LIVES)

ይህ ፕሮጀክት በአለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት ተነድፎ በካናዳ መንግስት የገንዘብ እገዛ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ሲሆን ሥራው እየተተገበረ ያለው ከአለም አቀፍ የውሃ ምርምር ኢንስቲትዩት፤ ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፤ ከኢትዮጵያ ግብርና ሚኒስቴርና ከክልል ግብርና ቢሮዎች፤ ከእንስሳት ሀብት ልማት ኤጀንሲ፤ ከክልሉ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትና ከሌሎች የልማት ፕሮጀክቶች ጋር በመሆን ነው፡፡

### የፕሮጀክቱ ዓላማ

በእንስሳትና በመስኖ እርሻ ልማት የሚተዳደሩት ሴትና ወንድ አርሶ አደሮችን ገቢ በዘላቂነትና አካባቢን በማይበክል መልኩ ማሳደግ ሲሆን ይንንም እውን ለማድረግ ገበያ ተኮር አመራረት ዘዴን መከተል፤ በእሴት ሰንሰለት ዙሪያ ያሉትን ዋና ዋና ተዋናዮችና ደጋፊ አካላትን ለይቶ አቅማቸውን መገንባት፤ ከገበያ ጋር ማስተሳሰር፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማላመድና ማስፋፋት፤ ጥሩ ተሞክሮዎችን መቀመርና ለተጠቃሚዎች ማዳረስ ቁልፍ ተግባራት ናቸው፡፡

### የፕሮጀክቱ ትግበራ ቦታዎችና የልማት ዘርፎች

የፕሮጀክቱ ሥራ በአራቱ ክልሎች (አማራ፤ኦሮሚያ፤ትግራይና ደቡብ ህዝቦችና ብሔር ብሔረሰቦች) በ10 ዞኖችና በ31 ወረዳዎች ይካሄዳል፡፡በአማራ ክልል በሦስት ዞኖች (ምዕራብ ጎጃም፤ ሰሜን ጎንደርና ደቡብ ወሎ) ስር በሚገኙ ዘጠኝ ወረዳዎች (ባህር ዳር ዙሪያ፤ሜጫ፤ይልማና ዴንሳ፤ ላይ አረማጭሆ፤ደመቢያ፤ ጎንደር ዙሪያ፤ተሁለደሬ፤ደሴ ዙሪያና ቃሉ) እየሰራ ይገኛል፡፡ትኩረት ተሰጥቶአቸው የተመረጡ የልማት ዘርፎች ወተት ሀብት ልማት፤ማድለብ፤ የበግና ፍየል ሀብት ልማት፤ ዶሮ ሀብት ልማት፤ ንብ እርባታ፤ በመስኖ የሚለሙ አትክልት፣ ፍራፍሬና መኖ ልማት ናቸው፡፡

### የወተት ሀብት ልማት

የወተት ሀብት ልማት በሁሉም የፕሮጀክቱ ወረዳዎችና ክልሎች ልዩ ትኩረት የተሰጠው ዘርፍ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የወተት ሀብት ልማትን ማሳደግ የማህበረሰብን ኢኮኖሚያዊ አቅምን ማጎልበት ብቻ ሣይሆን የስርዓተ ጾታን እኩል ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ፤ መላ ቤተሰብን የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኝ እድል በመስጠት በአካልና በአእምሮ የዳበረ ጤናማ አምራች ዜጋ ለመፍጠር የሚያስችል፤በርካታ የእሴት ሰንሰለት ተዋናዮችን ስለሚያሳትፍ ለብዙ ሰዎች የስራ እድልን የሚከፍትና የሀገሪቷን የምግብ ዋስትና በይበልጥ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ነው፡፡

### የቀን ወተት ፍጆታ/አጠቃቀም/ ፍላጎት

የአለም የጤና ድርጅት አንድ አዋቂ ሰው በቀን ሦስት ብርጭቆ ወተት በመጠጣት ለሰውነቱ አስፈላጊ ንጥረ ነገሮችን ሊያሟላ እንደሚችል ይገልጻል፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት የአንድ ሰው አማካይ ዓመታዊ የወተት ፍጆታ 200 ሊትር እንደሚሆን ይገምታል፡፡በአንዳንድ አገሮች ዓመታዊ ነፍስወከፍ የወተት ፍጆታ ከዚም በላይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለምሣሌ በፊንላንድ ዓመታዊ ነፍስወከፍ የወተት ፍጆታቸዉ 361.19 ሊትር ነው፡፡ በኢትዮጵያ ዓመታዊ አማካይ ነፍስወከፍ የወተት ፍጆታ 19 ሊትር ማለትም የአለም ጤና ድርጅት ከሚያዘው 8.5 ከመቶ ወይም በቀን 0.05 ሊትር ብቻ ነው፡፡ የጎረቤታችን ኬንያ አማካይ ነፍስወከፍ ዓመታዊ ፍጆታ 120 ሊትር ሲሆን የኛን ከ 6 እጥፍ በላይ ይሆናል፡፡

### ወተት ምንድን ነው?

- ወተት አጥቢ እንስሳት ልጆቻቸውን እንዲያሳድጉ ተፈጥሮ የለገሳቸው ተወዳዳሪ የሌለው በንጥረ ነገር የበለፀገ ሰውነታችን የሚፈልገውን ሁሉ በተመጣጠነ መልኩ የያዘ (all-in-one) ምግብም መጠጥም ነው፡፡
- ወተት አጥቢ እንስሳትና ሰዎች በህይወታቸው ዘመን የመጀመሪያ አፍ የከፈቱበት ምግብ ነው፡፡
- ወተት ለአጥቢ እንስሳትና ለሰዎች በህይወታቸው ዘመን የመጀመሪያ 'ክትባት' ነው፡፡ እንገር ከእናት ጡት የሚገኝ ከበሽታ ተከላካይና ምግብ ነው፡፡

*Milk is a Perfect Sole Diet'*

### የወተት ንጥረ ነገር ይዘት

የወተት የንጥረ ነገሮች ይዘት በርካታ ከመሆኑም በላይ በየጊዜው በሚካሄዱ ምርምሮች ተጨማሪ ይዘቶች እተለዩ ስለሆነ ጥቂቶችን ብቻ ጠቅሶ ማለፉ ተገቢ ነው፡፡

| ንጥረ ነገር | ለሰውነታችን የሚሰጠው ጠቀሜታ |
|---|---|
| ፕሮቲን | ሀሉንም ኢሴንሲያል ሚኖአሲዶችን በመያዝ ለአካል ግንባታ፣ ለተጎዳ አካል ጥገና |
| ቅባት | ኃይል ሰጪ |
| ካልሲየም | ለጥርስና ለአጥንት ጥንካሬና ጤንነት፤ለጡንጫዎች ሥራ፤ደም ያላግባብ እንዳይፈስ የማረጋት ሥራ |
| ፖታሲየም | የሰውነት ፈሳሽ መጠን መጠበቅ፤የደም ግፊትን መቆጣጠር፤ ለጡንጫ መለጠጥና መኮማተር |
| ፎስፈረስ | ለአጥንት ጥንካሬ፤ በሰውነት ህዋስ ውስጥ ኃይል ማመንጨት |
| አዮዲን | ለጤናማ እድገት፤የካልሲየምን ውህደት ማፋጠን፤ለቆዳችን ጤንነት፤ በሰውነት ህዋስ ውስጥ ኃይል ማመንጨት |
| ቫይታሚን A | ለዓይናችንና ለቆዳችን ጤናማ ሥራ፤በሽታ መከላከል |
| ቫይታሚን $B_2$ | የተመገብነውን ምግብ ወደ ኃይልነት መቀየር (catabolism) |
| ቫይታሚን $B_{12}$ | ለቀይ ደም ህዋስ መገምባት፤በሰውነታችን የኦክስጅን ዝውውርን ማሳለጥ |
| ኒያሲን | የኢንዛየሞችን ተግባር ማሳለጥ፤ የስኮርና ቅባቶችን ውህደት (metabolism) ማፋጠን |

## በቀን ቢያንስ ከ2 - 3 ኩባያ ወተት ይጠጡ